QuickNotes – ጁን 9/2021

## እየጨመሩ ስላለው የፀረ-ሰሚትክ ክስተቶች ምላሽ ጠቃሚ ሪሶርሶች

እየተካሄደ ባለው የእስራኤል-ፍልስጤም ግጭት ምክንያት በሞንትጎመሪ ካውንቲና በመላው አገሪቱ ላይ ረብሻ፣ የአመፅ ዛቻ፣ የአክራሪነትና የወግአጥባቂነት ፀረ-ሰሚትክ ስሜት መገለጫዎችን አስከትሏል። በእነዚህ ሪፖርቶች ምክንያት በተማሪዎችና በሠራተኞች፥ በተለይም በአይሁድ ተማሪዎችና በቤተሰቦቻቸው ደህንነት ላይ ስጋት ጨምሮባቸዋል። ተማሪዎች በትምህርት ቤት እንዲማሩ ሠላምና ደህንነት ሊሰማቸው ይገባል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማናቸውንም አይነት መድሎአዊነት፥ የዘረኝነት ጥላቻና ረብሻን፣ እንዲሁም በተማሪዎቻችን እና በሠራተኞቻችን በማህበረሰባችንም ላይ የሚቃጣውን የትኛውንም የዛቻና የማስፈራራት ሙከራዎችንና ድርጊቶችን በጽኑ ያወግዛል። ፍትኃዊነት፥ እኩልነትና አክብሮት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና እሴቶች ናቸው። ተማሪዎች እና ሠራተኞች እነዚህን እሴቶች እንዲጠብቁ እና የማህበረሰባችንን ብዝሃነት እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል ብዙ ሃይማኖታዊ እምነቶችን፣ ልማዶችን እና ባህሎችን ጭምር። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፍትህና እኩልነት ክፍል ሠራተኞች፥ ተማሪዎች እነዚህን ስጋቶች ተረድተው በእነዚህ ስጋቶች ዙርያ በጋራ እንዲሰሩ የሚረዳቸው ሪሶርስ አዘጋጅተዋል። ሪሶርሶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

ማንኛውም ተማሪ ዛቻና ማስፈራራት እንዲሁም ጥቃት ከደረሰበ(ባ)ት፥ እባክዎ ለሥራ ባልደረባ ያሳውቁ እና ይህንን ቅጽ ይሙሉ ስለ ማስፈራራት፥ ጥቃትና በደል የሚሞላ ቅጽ "bullying and harassment form"። የኃይማኖት ብዝሃነትን ስለማክበር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) መመሪያ ከዚህ በታች እንዲመለከቱ እናበረታታለን።

### ተዛማጅ ሪሶርሶች

- ድረገጽ፡- ማስፈራራት፥ ጥቃት፥ ወይም ዛቻን መከላከል
- ኦንላይን ስለ ማስፈራራት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ
- በወረቀት የሚታተም ስለ ማስፈራራት፥ ጥቃት፥ ወይም ዛቻ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

### ሃይማኖታዊ ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

- ኃይማኖታዊ ብዝሃነትን ስለማክበር መመሪያ (እንግሊዝኛ)
  ይህንን የመመሪያ ገጽ በሌሎች ቋንቋዎች ይመልከቱ

**ተጨማሪ ሪሶርሶች፡-** የትምህርት ባለሙያዎች እና ወላጆች ሊመለከቱት የሚገባ አገናኝ (ሊንክ)፡-

ስለ ፀረ-ሰሚትክ እና ዘረኝነት ማስተማርያ ቁሳቁሶች
የፀረ-ሰሚትክ መስፋፋትን ስለማስቆም ለወላጆች እና ለአስተማሪዎች 7 የማስተማርያ መንገዶች

ወላጆች ሊመለከቱት የሚገባ አገናኝ መረቦች (ሊንኮች)፦
ስለ ፀረ-ሴሚትስዝም ከልጆች ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚቻል
10,000 መኖራሃስ (Menorahs) በከተማዪቱ የጥላቻ ስሜትን ለማሸነፍ እንዴት መርዳት እንደቻሉ
ስለ ፀረ-ሰሚትስዝም ከልጆች ጋር ለመነጋገር 5 ፍንጭ የሚሰጡ ሃሳቦች
የጥላቻ ተምሳሌቶች

## የረዥም ጊዜ እቅድ የተማሪዎችን የሒሳብ አሠራር ችሎታ ሊያሻሽል ይችላል

በአገር አቀፍ ደረጃ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሒሳብ አፈጻጸም ላይ ከሌሎች የትምህርት መስኮች ሁሉ የላቀ ተጽዕኖ አሳድሯል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሂሣብ ፕሮግራም በሁሉም ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን ለመገዳደር የተነደፈ ነው። ግብ፦ ተማሪዎች በ 7ኛ፣ 8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል አልጀብራ 1 በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለከፍተኛ ደረጃ የሒሳብ ትምህርት እንዲዘጋጁ እንዲሁም ዓለም አቀፍ የባኩላሬት የላቀ ደረጃ ትምህርት ምደባ (International Baccalaureate classes) ጭምር እንዲዘጋጁ ማድረግ ነው።

የቨርቹወል ትምህርት መርሐ ግብርን ለማላመድና ከወረርሽኙ መጀመሪያ አንስቶ የተዛነፈ የትምህርት ይዘት እና ከሪኩለምን የመረዳት ፍጥነትን ለማስተካከል ሲባል ሆን ተብሎ ማስተካከያ ተደርጓል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይህን ሁኔታ ለማሻሻል የረጅም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቷል። ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች ይገኛል።

የሒሳብ - 2.5 ትምህርት መቋረጥ ችግሮችን -የማካካስ ዓመት እቅድ መግለጫ

የሒሳብ - 2.5 ትምህርት መቋረጥ ችግሮችን -የማካካስ ዓመት እቅድ

## የተማሪ አገልግሎት ትምህርት የመመረቂያ መስፈርት

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሠመር ወራት የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) እድሎች ላይ በመሳተፍ ለመመረቂያ መስፈርት የሚያስፈልጋቸውን የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓቶች ማሟላት ይችላሉ። በ SSL ድረገጽ ላይ የሚገኘውን በጊዜያዊነት የተሻሻለ መመርያ የሚከተሉ በርካታ በአካል እና ቨርቹወል/በርቀት የሙሣተፍ እድሎች አሉ SSL webpage በዚህ ወቅት አምስተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ከሐሙስ፥ ጁን 17 ጀምሮ በተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ዕድል መሳተፍ ሊጀምሩ ይችላሉ።

ተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች ይገኛል፦

| | |
|---|---|
| **ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት የሚከናወን የተማሪ አገልግሎት ትምህርት እድሎች**<br><br>የ MCPS SSL ድርጅቶችና እድሎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማእከል (MCVC) ድረገጽ ላይ የ MCPS SSL ዓርማና የመመረቂያ ቆብ መለያ ምልክት ተደርጎበታል | **ሁሉም እድሎች (ፊት-ለ-ፊት በአካል ጭምር)፡-** https://bit.ly/SSLOpportunities<br><br>**ቨርቹወል/የርቀት እድሎች፡-**<br><br>https://bit.ly/VirtualSSL2020 |
| **MCPS Form 560-50: Individual SSL Request Form**<br><br>ቀደም ሲል በሞንትጎመሪ ካውንቲ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማዕከል (MCVC) ዝርዝር ውስጥ ካልተካተተ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ጋር ለመሳተፍ ከአገልግሎት በፊት ቅድሚያ-ፈቃድ ለማግኘት ያገለግላል። | **የሠመር ወቅት አገልግሎት ለማጠናቀቅ ቅድሚያ ፈቃድ ለመጠየቅ፥** እባክዎ https://bit.ly/SSLPreApproval ሞልተው ለ SSL@mcpsmd.org ያቅርቡ። |
| **MCPS Form 560-51: SSL Activity Verification Form**<br><br>አገልግሎት ከተጠናቀቀ በኋላ የ SSL ሰዓትን ለማረጋገጥ እና ማስረጃ-ሰነድ ለመስጠት ጥቅም ላይ ውሏል<br><br>ተማሪና ተቆጣጣሪው ቅጹን መሙላት አለባቸው | **SSL Activity Verification Forms** https://bit.ly/SSLReflection **በሠመር ወቅት ለተጠናቀቀ አገልግሎት ፎል ላይ ለትምህርት ቤት የ SSL አስተባባሪ መቅረብ አለበት።** |
| **የተማሪ SSL ሪኮርዶች በ "Student/ParentVUE"**<br><br>የተማሪን SSL ሪኮርዶች በሙሉ በየደረጃው-የሚያሳዩ መመሪያዎች | **በየደረጃው የሚያሳይ መመሪያ** እዚህ ሊገኝ ይችላል https://bit.ly/SSLonVUE |
| **የ MCPS SSL ፕሮግራም መግለጫ**<br><br>የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) መስፈርቶች፣ መመሪያዎች፣ ሂደቶች፣ ሽልማቶችና ቅጾች አጠቃላይ ይዘት | **የ MCPS SSL ፕሮግራም መግለጫ** እዚህ ይገኛል https://bit.ly/SSLOverview2020 |

የትምህርት ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት ስለ ተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL) ፕሮግራም ማናቸውም ጥያቄ ካለህ(ሽ)፥ ለትምህርት ቤት የ SSL አስተባባሪ ኢሜይል አድርግ(ጊ) ለ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና ለ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች። በሠመር ወቅት ስለ SSL ፕሮግራም ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት፥ ወደ MCPS SSL ቢሮ ኢሜል ያድርጉ።

### ያስታውሱ፦ ለ 2021-2022 የትምህርት ዓመት የመዋእለ ህጻናት ምዝገባ ተጀምሯል

ለ 2021-2022 የትምህርት ዓመት ልጆቻቸውን በ MCPS መዋእለ ህጻናት እንዲማሩ ማስመዝገብ ለሚፈልጉ ወላጆች ምዝገባ ተጀምሯል። የሚመዘገቡት ልጆች በሴፐተምበር 1/2021 ወይም ከዚያ በፊት 5 ዓመት እድሜ ሊሞላቸው ይገባል። ብቁ ስለመሆን መመሪያ፣ ስለ ምዝገባ፣ ወይም ማመልከቻ ለመሙላት አስፈላጊ ሠነዶችን በሚመለከት የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 240-740-4530 ይደውሉ ወይም የ MCPS ድረገጽ ይጎብኙ።

የምዋእለ ህፃናት ምዝገባ (Kindergarten Registration)

### ለ 10ኛው ዓመታዊ "Annual Give BACKpacks Campaign" ዘመቻ ድጋፍ ይስጡ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የገንዘብ እርዳታ እና በቦርሳ ታጭቆ የሚሰጥ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶችን በመሰብሰብ በ MCPS ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ተማሪዎች ለማከፋፈል 10ኛውን ዓመታዊ የ "Annual Give BACKpacks Campaign" ዘመቻ ስንጀምር ከእኛ ጋር ይሳተፉ።

$10 ዶላር በመለገስ ለአንድ ተማሪ በቦርሣ የታጨቀ የትምህርት ቁሳቁሶችን መስጠት ይችላሉ። በትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ በተቻለ መጠን ለበርካታ ተማሪዎች የት/ቤት ቦርሣ (backpack) እና የትምህርት ቁሣቁሶችን የመስጠት ግብ በመያዝ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሠመር ወቅት ማቴሪያሎችን ያዛል። የትምህርት እቃዎቹን ለማዘዝ ጁን፣ ጁላይ፣ እና ኦገስት በጣም ወሣኝ ወሮች ናቸው።

በ2020-2021 ዘመቻ፥ በማህበረሰባችን የሚገኙ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ልግስና ምስጋና ይድረሳቸውና ዲስትሪክቱ የትምህርት ቁሳቁስ ለሚያስፈልጋቸው ከ26,000 ለሚበልጡ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን ድጋፍ ሰጥቷል። በዚህ ዓመት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ቤቶቻችን ለሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶችን እና በጀርባ የሚይዙትን ቦርሳዎች ለመግዛት $300,000 ዶላር የማሰባሰብ ግብ አስቀምጧል።

ስለ ዘመቻው ለሌሎች በማሰራጨት ይርዱን። የዘመቻውን በራሪ ጽሑፍ ለስራ ባልደረቦች፥ ለቤተሰብ፥ ለጓደኞች እና ለማህበረሰብ አባላት በማሠራጨት ያግዙን። እያንዳንዱ ልግስና ድጋፍ የሚያስፈልገውን/የሚያስፈልጋትን ተማሪ ይረዳል።

ስለ "Give BACKpacks" የበለጠ ግንዛቤ ያግኙ።

**ለጦር መሣሪያ ባለቤቶች ስለ ብሔራዊ የደህንነት ወር ማሳሰቢያ**

በሞንትጐመሪ ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ ሪፖርት መሠረት፥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ እና በመላው አገሪቱ የጦር መሣሪያ ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። ይህ ወር ስለ ዩ.ኤስ ብሔራዊ ደህንነት የሚታሰብበት ወር እንደመሆኑ፥ ቤተሰቦች የጦር መሣሪያዎቻቸውን ለደህንነት በማያሰጋ አስተማማኝ ሁኔታ ማስቀመጥ እንዳለባቸው እና ስለ ሽጉጥ/ጠመንጃ አያያዝና ደህንነት ከልጆቻቸው ጋር ጠቃሚ ውይይት እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። Project ChildSafe እና Alliance for Gun Responsibility የመሣሰሉ ድርጅቶች ለወላጆች፥ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ባለሙያዎች ስለ ጦር መሣሪያ ደህንነት እና የጠመንጃ-ሽጉጥ ረብሻን ስለመከላከል በርካታ ሪሶርሶችን ይሰጣሉ።

**የካውንቲው የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት 13 ቅርንጫፎችን እንደገና ለመከፈት ተዘጋጅቷል**

የሞንትጐመሪ ካውንቲ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ማክሰኞ፣ ጁን 1 ቀን ስድስት ቅርንጫፎችን የከፈተ ሲሆን፤ ጁን 14 ደግሞ ተጨማሪ ሰባት ቅርንጫፎችን ይከፍታል። ከጀርመንታዎን ቤተ መጻሕፍት (ለዕድሳት ዝግ ይሆናል) እና "Noyes Library" የልጆች ቤተ መጻሕፍት በስተቀር የተቀሩት ቅርንጫፎች በሙሉ ጁላይ 6 እንደገና ይከፈታሉ።

በሁሉም ቅርንጫፎች የአገልግሎት መስጫ ሰዓቶች ሰኞ፣ ረቡዕ፣ ዓርብ፣ እና ቅዳሜ ከ 10 a.m. እስከ 6 p.m. ሲሆን ማክሰኞ እና ሐሙስ ከእኩለ ቀን እስከ 8 p.m. ይሆናል። ተጨማሪ መረጃ እንደተገኘ በ MCPL ድረገጽ ላይ ይገለጻል።

ተጨማሪ ግንዛቤ ያግኙ